


# የአማራ ማሕበር በጀርመን ከተመሰረተ 10 ዓመት ሆነው

**በማንነቱ የሚጠቃ ሕዝብ ፣ የግድ በማንነቱ ተደራጅቶ ለህልውናው መታገል አለበት!**

የአማራ በማንነቱ መደራጀት ተፈጥሮአዊ መሆኑ ዛሬ በሰፊው ተቀባይነትን አግኝቷል። የዛሬ 10 ዓመትና ከዚያም በፊት ሁኔታው ከዛሬው የተለየ ነበር። አማራው በኅሳ ፋሽስቶች ሲጨፈጨፍ **„እኔ በኢትዮጵያዊነት እንጂ በጎሳ አላምንም“** በማለት ሰምቶ እንዳልሰማ የተኛው አማራ ስፍር ቁጥር አልነበረውም። የአማራ ማሕበር በጀርመን (**Verein der Amhara in Deutschland e.V. VAD**) ከተቋቋመ እነሆ 10 ዓመት ሆነው። በአለፉት 10 ዓመታት የአማራው የህልውና ትግል እንዲሰምር ማሕበራችን የተቻለውን ሁሉ አድርጓል። አማራው ተደራጅቶ ለሕልውናው እንዳይታገል ለመበታተን ይሰሩ የነበሩትን ባንዳዎችና ፀረ አማረ ኀይሎች ፣ በተለይ የአስመሳይ ኢትዮጵያውያንን አሻጥር በመቋቋም መስራች አባሎች ለአደረጉት የተሳካ ተጋድሎ እናደንቃቸዋለን።

ከጅምሩም፣ ማሕበራችን የተቋቋመው በጀርመን የሚኖረውን አማራ አስተባብሮ በተጠናከረ አማራዊ አንድነት የተጋረጠብንን የህልውና አደጋ ለመቀልበስ ለሚታገሉ ድርጅቶች በምንችለው ሁሉ ድጋፍ ለመስጠት ነበር። ይሄ ዓለማችን ዛሬም እንዳለ ነው። በሌላ በኩል ዛሬ በተለያዩ የጀርመን ከተሞች ከ8 የሚበልጡ የአማራ ማሕበራት ተመስርተዋል። ይሁን እንጂ እነዚህን ማሕበራት በአንድ ጥላ ስር አድርጎ የተቀናጀና ጠንካራ እንቅስቃሴ ማድረግ አልተቻለም። ማሕበራችን ጀርመን የሚኖረውን አማራ ለማደራጀት ያላሰለሰ እንቅስቃሴ እያደረገ ቢሆንም አማራውን በአንድ ጥላ ስር የማድረጉ እንቅስቃሴዎች በበቂ ግባቸውን አልመቱም። ላለመሰባሰብ ምክንያት ይሆናሉ ያልናቸውን ዝርዝረን ወደፊት ለማቅረብ የምንሞክር ቢሆንም በዚህ ፅሑፋችን ላይ በአንድ ማድረግ እንቅስቃሴዎቻችን ላይ በሁሉም ሙከራችን ከታዘብናቸው እውነቶች ወናውን እናንሳ። በሁሉም ማሕበሮች በሚባል ደረጃ ውስጥ የአማራውን(የፋኖን) የህልውና ትግል ለመደገፍ ከእኛ ማሕበር እኩል የሚጥሩ አማሮች እንዳሉ ተገንዝበናል። ሆኖም ማሕበራችን እንደ አንጋፋነቱ እነዚህን አማሮች ይዞ በጀርመን ደረጃ የአማራውን እንቅስቃሴ ለማቀነባበር አልተቻለውም። በውስጣችን እንደተከፋፈልን እንድንቆይ የሚሰሩት ባለተልኮዎችና የግል ጠባያቸው ለማሕበራዊ ሥራ የማይመች ግለሰቦች አስተዋፅዖ እንዳለ ሆኖ **ዋናው ድክመታችን ግን፣ የጀርመኑን አማራ የሚቀሰቅሱ ቋሚ ሥራዎችን አለመስራታችን ነው።** ለምሳሌ በአለፉት ዓመታት በጀርመንኛና በእንግሊዝኛ ያወጣናቸው ጽሑፎች በተወሰነም ደረጃ ቢሆን በአማራው ውስጥ የመሰባሰብ ፍላጐት ጨምሮ እንደነበር አባል ያልሆኑ አማሮች ነግረውናል።

በአድቮኬሲው ሥራ ላይ ውጭ ያሉትን የአማራ ጠላት ማሕበሮች ፀረ አማራ መግለጫዎች, „ሕብረት“ ወዘተ ማጋለጥ „የዕለት እንጀራችን“ መሆን ነበረበት። ጠላቶቻችን በምዕራባውያን እየተረዱ የአማራን ታሪክ ፣ ባህል ወዘተ በማጥፋት የሐሰት ትርክቶችን በመፈብረክ በአማራው ላይ የሚደረገውን የዘር ማጥፋት ዘመቻ በመካድና እንዳይታወቅ በመሸፋፈን እንቅስቃሴዎቻቸውን ቀጥለዋል። እነጀዋር መህመድ፣ሳይቀሩ የኦሮሞ ኤሊቶች ፋኖ በቢዛሞ የሚየደደርገውን የሕልውና ትግል እንዲወገዝ ጥሪ እያደረጉ ነው። ይህንና መሰል የጠላቶቻችንን ፕሮፓጋንዳ ለማክሸፍ በማሕበር ደረጃ የተከናወነ እንቅስቃሴ የለንም ማለት ያስደፍራል። አውጭ ያሉት የጠላት ኤሊቶች „ኢትዮጵያን ከአብይ አገዛዝ ተባብረን እናድናት“ በማለት ከቅጥረኛ ባንዳዎች ጋር ሆነው „ሕብረት መሠረትን“ ሲሉ ማሕበራችን የተቃውሞ ጽሑፍ ማውጣት ነበረበት። **ማሕበራዊ አንድነት ብቻውን አቋምን አይገነባም። አንድ ዓይነት አቋም ያላቸው ግን አንድነትን ይገነባሉ፣ይሰባሰባሉ።** ማሕበራዊ አንድነትና ጥንካሬ የሚለካው ፣ አባላቱን እየጨመረ የሚሄደው በሚያደርገው እንቅስቃሴ ጥራትና ብዛት ነው። በመሆኑም ጀርመን ውስጥ ያሉትን የአማራ ስብስቦች በሽማግሌ፣አንድ ለማድረግ መሞከር ውጤት አልባ እንደሚሆን እርግጠኞች ነን። **እንወቅ**! የአማራው መጨፍጨፍ የሚያንገበግባቸው የጀርመን አማራዎችን ልንስብ የምንችለው በምናደርገው አስተዋፅዖ አሳማኝነት ነው። በመሆኑም ለህልውናው ትግል አሳማኝና ቀጣይነት ያለው አስተዋፅዖ ለማድረግ በርትተን እንስራ።

በዚህ አጋጣሚ አዲሱን የማሕበራችንን ድህረ ገፅ https://amhara-association-germany.de/startseite ለአንባቢዎቻችን በድጋሜ ማስተዋወቅ እንወዳለን። ከዚህ በኋላ ቀጣይነት ባለው መንገድ የተለያዩ ፅሑፎችን በድህረ ገፃችን እያወጣን የምናሰራጭ ይሆናል። እያንዳንዳችን ድሕረ ገፁ ሰፊ ተደራሽነት እንዲኖረው ማገዝ ይጠበቅብናል።